## ፓትርያርክ ጳውሎስና ያስፈጁቸው ሊቃነ ጳጳሳት

ገብረ ኪዳን

የፓትርያርክ ጳውሎስን ሞት ተከትሎ ፣ ታዋቂው ደራሲና ሰባኪ ዲያቆን ዳንኤል ክብረት "ለምጣዱ ሲባል አይጧን " በሚል ርእስ ፣ አጭር ግን ጠንካራ መልእክት ለመላው ኢትዮጵያውያን አስተላልፎ ነበር ። የጽሁፉም ዋና ጭብጥ አንድና ግልጽ ነው--- " ለቤተ ክርስትያኒቱ ክብር ሲባል ለተወሰኑ ቀናት ስለ ፓትርያርኩ ክፉ ስራና ደካማ ጎኖች የሚያትቱ ጽሁፎችም ሆነ ውይይቶች አንዲዘገዩ " የሚማጸን ነበር ። ለቤተ ክርስትያኗ ክብር ሲባል መራሄ ቤተ ክህነቱ አቡነ ጳውሎስ ከበቂ በላይ የሀዘን ( ይገባቸዋል ብዬ ባላምንም) ስርአት ተካሂዷል ። እነሆ አሁን በዘመናቸው ስለተከናወኑ አሰቃቂና አስጸያፊ ወንጀሎች እናውሳ።

ሟች ፓትርያርክ ጳውሎስ ይወቀሱበትና ይከሰሱበት የነበሩት ወንጀሎች ብዙ ናቸው። በሃይማኖት ጉዳይ አለቃ አያሌው በመፍቀሬ ካቶሊክነት ሲወቅሷቸው ፣ አቡነ አብርሃምና ሌሎች በርካታ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃነ ጳጳሳት ደግሞ ጥንተ አብሶን በተመለከተ ፓትርያርኩ በመመረቂያ ጽሁፋቸው ላይ በጻፉት ኢ - ኦርቶዶሳዊ ትምህርት አንቀው ይዘዋቸው ነበር። በገንዘብ አባካኝነትና በሙስና ሲወቀሱ የነበሩት ፓትርያርክ ጳውሎስ ፣ ህይወታቸው ሲያልፍ በዘመዶቻቸው አካውንት አስከፍተው ያስቀመጡት 22 ሚሊዮን ብር መገኘቱ በሙስና የሚቀርብባቸውን ወቀሳ እውነተኛነት ያመላክታል። ሌሎችም ብዙ መረጃና ማስረጃ የተገኘባቸው ክፉ ስራ ቢኖራቸውም እኔ ግን የትኩረት ነጥቤ የሳቸውን ስልጣን ከመጠበቅ ጋር በተያያዘ በምስጢር የተገደሉትን የሊቃነ ጳጳሳትና የሊቃውንተ ቤተ ክርስትያን ህይወት ይመለከታል።

### የሊቃነ ጳጳሳቱ እልቂት በወፍ በረር እይታ

ፓትርያርክ ጳውሎስ በህይወት በነበሩ ዘመን ያካሂዱ የነበረውን ኢ ቤተክርስትያናዊ አካሄድ አምርረው የተቃወሙ ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንተ ቤተ ክርስትያናት በርካታ ነበሩ። በሚያስገርምና ሚስጥራዊ በሆነ ሁኔታ ግን እሳቸውን አምርረው የተቃወሙ ጳጳሳትና ሊቃውንት ህይወታቸው አልፏል። የባሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ሰላማ ፣ ፓትርያርክ ጳውሎስን ክፉኛ ተቃውመው የነበሩ ቆራጥ አባት ነበሩ። ከሳቸው( ከፓትርያርኩ) ጋር ጸብ በጀመሩ በጥቂት ግዜያት ውስጥ አቡነ ሰላማ አረፉ ተባለ ። አሟሟታቸው እንግዳ ነበር ። በ2001 ዓ.ም የፓትርያርኩን አምባገነናዊ አካሄድ ክፉኛ በመቃወም ፓትርያርኩ ስልጣናቸው እንዲቀነስና እንዲገደብ ታላቅ ትግል አድርገው የነበረው አቡነ መልከጼዲቅም በጥቂት ግዜያት ውስጥ አረፉ ። የርክበ ካህናት ስብሰባ ላይም የሲኖዶሱ አካሄድ ውሃ ወቀጣ እየመሰለ እንደመጣና ፓትርያርኩ ለሰው ከሚያደሉና ከሚገዙ ለእግዚአብሔር ቢያደሉ የተሻለ እንደሆነ በመጥቀስ ፓትርያርኩን ክፉኛ የተናገሯቸው አቡነ በርናባስም አስገራሚ በሆነ ሁኔታ በድንገት መሞታቸው ታወጀ ።የነዚህን ሊቃነ ጳጳሳት ሞት ልዩ የሚያደርገው ጳጳሳቱ የሞቱት ከአቡነ ጳውሎስ ዛቻ በሁዋላ መሆኑ ሲሆን የሁሉም ሊቃነ ጳጳሳት ሞት ምክንያት የሆድ ህመምና የጉበት መመረዝ መሆናቸው ነው። ጉዳዩ የበለጠ አስገራሚ የሚሆነው ደግሞ ሁሉም የሞቱት ምግብ ተጋብዘው ከበሉ በሁዋላ ባደረባቸው ከባድ ህመም መሆኑ ነው። ዝርዝሩን ከመሰረቱ በማስረጃ እንመልከት

**2001 ኢ.ም እና የፓትርያርክ ፓውሎስ ስልጣን መነቃነቅ**

የ2001 ዓ.ም የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ፓትርያርክ ፓውሎስን በመረረና በከበደ ሁኔታ ነበር የወቀሳቸው። ሲኖዶሱም ፓትርያርኩን ከመውቀስ ባሻገር ስልጣናቸውን የሚገድብ ውሳኔ አሳለፈ። በግንቦት ወር 2001 ዓ.ም የወጣው አዲስ ነገር ጋዜጣ ሁኔታውን እንዲህ ሲል ነበር የዘገበው

> *በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባዔዎችም ሆነ በሌሎች አጋጣሚዎች በፓትርያርኩ ላይ "ይህን የመሰለ ግልጽና የተብራራ ወቀሳ ቀርቦ አያውቅም" ያሉት ምንጮች እንደሚያስረዱት የውይይት ሐሳብ ያቀረቡት ሊቃነ ጳጳሳት በርካታ ጉዳዮችን ማንሣታቸውን ገልጸዋል። ሐሳብ አቅራቢዎቹ በጉባዔው ላይ እንደተናገሩት ከሆነ የቀድሞውን ፓትርያርክ ጨምሮ አሜሪካ በሚገኙት እና አገር ቤት ባለው ዋናው ሲኖዶስ መካከል የተፈጠረው ችግር እንዳይፈታ እንቅፋት የሆኑት ፓትርያርኩ ናቸው ብለዋል። ፓትርያርኩ ያለ ቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ ሊቃነ ጳጳሳትን ከአንዱ አገረ ስብከት ወደ ሌላው ያዛውራሉ፤ የቤተ ክህነቱን ውራ አስኪያጅ ስልጣን በመጋፋት በተለያዩ ሃላፊነቶች ላይ የሚገኙ ሰዎችን ሾመዋል፣ ሽረዋል፣ ቀጥረዋል፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን ሚዲያዎች ግልጽ አሠራርና ኤዲቶርያል ፖሊሲ የሌላቸው የግል መጠቀሚያ አድርገዋቸዋል፣ አሠራሩ ከሚፈቅደው ውጪ በግል ትእዛዛቸው ገንዘብ ሠጪ አድርገዋል የሚሉት ወቀሳዎች ለሲኖዶሱ ከቀረቡት በርካታ ሐሳቦች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። ሐሳብ አቅራቢዎቹ ቅ/ፓትርያርኩ ያለ ቤተ ክርስቲያኒቱ ሕጋዊ ፈቃድ አሜሪካ ለሚገኘው "የሀገር ፍቅር ሬዲዮ" አዘጋጅ አንድ መቶ ሺህ ብር እንዲሰጥ ማድረጋቸውን ከመጥቀሳቸውም በላይ በአሁኑ ወቅት ቤተ ክርስቲያኒቱ በከፍተኛ የገንዘብ ችግር ውስጥ እንደምትገኝ ለጉባዔው አስረድተዋል። ቤተ ክርስቲያኒቱ ያሏት ተከታዮች ብዛትና ግዴታ ያህል የሚጠበቅባትን እያበረከተች አለመሆኑን የገለጹት ሐሳብ አቅራቢዎቹ መሠረታዊ የሥራር ለውጥ ልታካሂድ እንደሚገባት መጠየቃቸውም ታውቃል* [i]

ሜይ 28 2009 ኢትዮ ሚዲያ ፎረም ባወጣው ዘገባ ላይ ደግሞ ፓትርያርኩ ከስልጣናቸው እንደተወገዱና በስልጣን ዘመናቸውም ስልጣናቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ ስላስፈጀ፟ቻው ጳጳሳት እንዲህ ሲል ዘገበ

> *Week-long session was held by the Holy Synod from 14 to 29 May 2009, which passed the resolution to avoid Abune Paulos from his power.Reports from EOC also confirm that Abune Paulos has eliminated many of his opponents. Among the bishops removed by Aba Paulos include Abune Matias, Abune Yoseph, Abune Petros and Abune Elias. They all are dead in a misterious way. Paulos' bodyguards have also gunned down a priest inside a church in Addis Ababa.* [ii]

**የፓትርያርኩ ዛቻ**

ፓትርያርክ ጳውሎስ ግን ቅዱስ ሲኖዶሱ የጣለባቸውን እግድና ማእቀብ በጸጋ አልተቀበሉትም። ለሲኖዶሱ አባላት ይልቁንም እሳቸውን አጥብቀው ለተሟገቷቸው ጳጳሳት የሰጧቸው መልስ " ወዮላችሁ ጉዳችሁ ይፈላል " የሚል ነበር ።

> *ቤተ ክርስቲያንን በሙስና (ኮራፕሽን) ዘፍቀዋል፣ ክብሯን አዋርደዋል፣ አንድነቷን አደጋ ላይ ጥለዋል፣ ሚዲያዎቿን ለግል ጥቅማቸውና ጠላቶቻቸውን ለማዋረድ ተጠቅመውበታል ያላቸውን ፓትርያርኩን "ከቡራኬ ውጪ" በየትኛውም ዓይነት አስተዳደርና የሹመት ሥራዎች ውስጥ እንዳይገቡ አግዷቸዋል። በቤተ ክርስቲያኒቱ የቅርብ ዘመን የአባቶች ታሪክ ውስጥ ታይቶና ተሰምቶ በማያውቅ መልኩ በመንፈሳዊ አርበኝነት ፓትርያርኩን የተቋቋሟቸው ብፁዓን አባቶች እንደቀድሞው ለማስፈራራት፣ "ጉዳችሁን ነው የማፈላው" ያሉትን ፓትርያርክ ሳይፈሩ በመንቀሳቀስ ቤተ ክርስቲያኒቱ "አበቃላት፣ አከተመላት" የተባለው የተቀናቃኞቿን ጉራ የሚያከሽፍ ተግባር ፈጽመዋል።* [iii]

## የፓትርያርኩ "ጉዳችሁን ነው የማፈላው" ዛቻ ተከትለው የተፈጸሙ ወንጀሎች

የፓትርያርኩ ዛቻ ግን መሬት ወድቆ አልቀረም። የሲኖዶሱ አባላት ውሳኔውን በወሰኑ እለት ማታ በፓትርያርኩ ላይ ጠንካራ ተቃውሞ በማቅረብ ውሳኔው እንዲወሰን ያደረጉ አባቶች ቤት ሌሊት ባልታወቁ ሰዎች ተሰበረ። ታፍነውም የተወሰዱ አሉ። በግዜው የነበረውን ሁኔታ ደጀ ሰላም የተባለው ድረ ገጽ እንዲህ ዘግቦት ነበር።

> *ዛሬ ረቡዕ ከምሽቱ አራት ሰዓት ጀምሮ በአካባቢው ያለውን የመብራት መጥፋት ተገን ያደረጉ ሰዎች በብፁዓን አባቶች ላይ አደጋ መጣሉ ተሰማ:: የደጀ ሰላም ምንጮች እንደተናገሩት ከምሽቱ 4 ሰዓት እስከ 5 ሰዓት ባለፈው ጊዜ ማንነታቸው ለጊዜው ያልታወቀ ሰዎች የብፁዓን አባቶችን መኖሪያ በመደብደብ፣ በር ገንጥሎ በመግባት አደጋ ለማድረስ መሞከራቸው ሲታወቅ ይህ ዜና በተጠናቀረበት ወቅት አባቶች ላይ የደረሰው አደጋ ምን እንደሆነ፣ የተጎዱትስ አባቶች ምን እንደገጠማቸው አልታወቀም። ምንጮቻችን እንደተናገሩት ብፁዕ አቡነ ኤጲፋንዮስ ሳይሆኑ አይቀሩም፣ ሲጮሁና "አድኑኝ" ሲሉ ተሰምተዋልተብሏል። ፓትርያርኩን በመቃወሙ ዘርፍ ስብሰባዎችን ሲመሩ የሰነበቱት የብፁዕ አቡነ ቄርሎስ መኖሪያ በር ከተሰበረ በሁዋላ ብፁዕነታቸው የመኝታ ቤታቸውን በር ቆልፈው ከአደጋው አምልጠዋል ተብሏል። ማንነታቸውን ለጊዜው ያላወቅነው አንድ አባት ግን ችግር ሳይደርስባቸው አልቀረም። እኚሁ አባት "ብፁዕ አቡነ ኤጲፋንዮስ ናቸው፤ ታፍነው ሳይወሰዱ አልቀሩም" ሲሉ ምንጮቻችን ጥቆማ ሰጥተዋል። የዛሬው አደጋ ኢላማ የሆኑት አባቶች የፓትርያርኩ ተቃዋሚዎችና በዛሬው ስብሰባ ላይ ጠንካራ ሐሳብ የሰነዘሩት ናቸው ተብሏል።* [iv]

## የብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ  ሕክምና ሞት

ከጥቂት ግዜያት በኋላም ፤ በሲኖዶሱ ስብሰባ ላይ በጠንካራው አባ ጳውሎስን ሲቃወሙ የነበሩትና ይህንንም በማድረጋቸው በፓትርያርኩ ደጋፊዎች በሌሊት ቤታቸው የተደበደበው አቡነ መልኬጼዲቅ በድንገት መታመማቸው ተሰማ:: ህመማቸውም ከምግብ መመረዝ ጋር በተያያዘ የጉበት በሽታ እንደሆነ በሰፊው ተወራ:: ብዙም ሳይቆዩ ከተወሰኑ ወራት በኋላ ማረፋቸው ተሰማ::

> *የጉራጌ፣ ሀድያና ስልጢ አህጉረ ስብከት ሊቀጳጳስ የሆኑት ብፁዕነታቸው በጉበት ካንሰር በሽታ ሲታከሙ ቆይተው ዛሬ ሌሊት አርፈዋል። አስከሬናቸውም ዛሬ ወደ ታላቁ የምሑር ገዳም የተሸኘ ሲሆን ሥርዓተ ቀብራቸውም ነገ ማክሰኞ ይፈጸማል። ብፁዕነታቸው በታታሪነታቸው ከሚመሰገኑ አበው መካከል አንዱ ሲሆኑ ባለፈው ዓመት በቤተ ክህነቱ በተነሣው የሕገ-ቤተ*

*ክርስቲያን ይከበር ጥያቄ ሐምሌ 8 ቀን 2001 ዓ.ም መኖሪያቸው ከተደበደበውና አደጋ ከተጣለባቸው ብፁዓን አባቶች መካከል አንደኛው መሆናቸው ይታወሳል።* [v]

የአቡነ መልከጼዲቅን ማረፍ ተከትሎ አዲስ አበባ ላይ ሲወራ የነበረው ሊቀ ጳጳሱ በግፍ እንደተገደሉ ነው። ዜናውን መጀመርያ ይዛ በወጣችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ድረ ገጽ ደጀ ሰላም ላይም የተሰጡ አስተያየቶች ይህንኑ የሚያጠናክሩ ናቸው። " anonnymus ሚስጥር አዋቂ "በሚል መጠርያ አስተያየት የሰጡ አንድ ግለሰብ በሳቸው ሞት ዙርያ investigative journalism ይካሄድ እስከማለት ደርሰው ነበር

*Anonymous said...*

*ጁላይ 15,2009 የወጣው የደጀ ሰላም ዘገባ ይህ ነበረ።*
*""(ሰበር ዜና፣ Breaking News) ብፁዓን አባቶች ላይ አደጋ ተጣለ"*
*ከዚያን ግዜ ጀምሮ በርካታ አባቶች ችግር እየደረሰባችው ነው። ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ በከባዱ ታመው ሀኪም ፍለጋ ውጭ ህደው ታከሙ። የጉራጌ፣ ሀድያና ስልጢ አህጉረ ስብከት ሊቀጳጳስ የሆኑት ብፁዕነታቸው አባታችንም አቡነ ጳውሎስን ከሚቃወሙ ወገኖች መካከል አንዱ ነበሩ።ወዲያው በጉበትና ካንሰር በሽታ ታመሙ ተባለ።አዲስ አበባ ውስጥ ውስጡን የሚወራው አባታችን የሞቱት በደባ መሆኑን ነው።ከምግብ ጋር በተሰጠ መድሀኒት መታመምና መሞታቸው ይናፈሳል።ደጀ ሰላሞች ባካችሁ ጦማራችሁሚስጥር ልታገኝ ስለምትችል investigative journalism ብታካሂዱ።*
*ሚስጥር አዋቂ*

**ያቡነ በርናባስ ፓትርያርኩን አጥበቀው መቃወምና ድንገተኛ እረፍታቸው**

ከግንቦት 10-16 ,2003 ዓ.ም የተካሄደው የርክበ ካህናት ቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ላይም ባባ ጳውሎስ ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ ተነስቶ ነበር። የግንቦቱን ተቃውሞ ልዩ የሚያደርገው ባባ ጳውሎስ ላይ የከረረ ትችትና ተቃውሞ ያቀረቡት ከዚህ በፊት ድምጻቸው ተሰምቶ የማያውቁት አቡነ በርናባስ ነበሩ። ብጹእነታቸው የሲዳሞ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ሆኖ በፓትርያርኩ አላግባብ በተሾመው ጌታቸው ዶኒ ላይ የተደረሰበት ውሳኔ እንዳይረጋ አቡነ ጳውሎስ የጉባኤውን አመራር ውኃ ቅዳ ውኃ መልስ ያደረጉበትን አካሄድ ተቃውመዋል፤ *‹‹የሲኖዶሱ አካሄድ ውኃ ወቀጣ ሆኗል፤ ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር፣ ከግለሰብ ይልቅ ለቤተ ክርስቲያን መወገን አይሻልም ወይ?››*በማለት ፓትርያርኪን በግልጽ ነቅፈው ተሰብሳቢውንም እግዚአብሔርን እንጂ ፓትርያርኩን ሳይፈሩ አባ ጳውሎስ ያቀረቡትን ንድፈ ሀሳብ እንዲቃወም አስተባብረዋል። እጅግ የሚደንቀው ግን ይሄንኑ ተቃዎሞ ባካሄዱ ምሽት የበሉት ምግብ አልተስማማቸውም ተብሎ ታመሙ። በሚቀጥለው ቀን ስብሰባ ላይ እንኳን መገኘት አልቻሉም።ያስጀመሩትን አጅንዳ እንኳን መጨረሻውን ሳያዩ ከዚህ አለም በሞት ተለዩ።

*ብፁዕነታቸው በባሕር ዳር መንበረ ጵጵስናቸው ቅዳሜ ግንቦት 20፣ ከቀኑ 8፡00 ላይ ከደረሱ በኋላ ከምሽቱ 3፡00 ላይ ማረፋቸውን የስፍራው ምንጮች ተናግረዋል፡፡ ብፁዕነታቸው የሰነበተ ሕማም እንደሌለባቸው፣ ግንቦት 16 ቀን የነበረውን የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ የመጨረሻ ቀን ውሎ ‹‹ሆዴን አሞኛል›› በማለታቸው ሳይሳተፉ መቅረታቸው ተጠቁሟል፡፡ ረቡዕ ግንቦት 17 ቀን ወደ ሕክምና የተወሰዱት ብፁዕነታቸው ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሪፈራል ተጽፎላቸው የነበረ ቢሆንም ‹‹ግዴለም፤ እዚያው ቤቴ ውሰዱኝ፤ ባሕርዳር ስደርስ እታከመዋለሁ›› በማለታቸው መንገድ መግባታቸውን እኒሁ ምንጮች ያስረዳሉ፡፡* [vi]

**የአቡነ ቄርሎስ ሽሽትና ምስጢራዊ ህክምና**

“ለሕይወቴ ደህንነት አይሰማኝም”:- አቡነ ቄርሎስ

እየተካሄደ ያለውን የበቀል ዱላና ስራት አልበኝነት የተረዱት አቡነ ቄርሎስ የቤተ ክህነቱን ግቢ ለቀው ግለሰብ ቤት በመሰንበት ህይወታቸውን ለማዳን ቢችሉም እሳቸውም ፤ ከዚያን ግዜ በኋላ ጤነኛ ሆነው አልታዩም። እንደ ብዙዎች ስጋት ከሆነ አደጋ ጣዮቹ ቤታቸውን በሌሊት በሰበሩበት ወቅት ቅዱስነታቸውንም አካላዊ ጉዳት ሳያደርሱባቸው( ምንም እንኳን እሳቸው ለመናገር ፈቃደኛ ባይሆኑም) እንዳልቀረ ይገመታል። ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው ክስተቱ በተፈጸመ በጥቂት ግዜያት ውስጥ ወደ ታይላንድ ለህክምና መሄዳቸው ነው። በግዜው የነበረውን የሳቸውንም ጉዳይ ደጀ ሰላም እንዲህ ዘግባው ነበር

> *በማፊያ ቡድን አባሎችና ወረበሎች መኖሪያቸው የተሰባበረባቸውና በሕይወታቸው ላይ አደጋ የተቃጣባቸው አረጋዊው አባት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ለደህንነታቸው በመስጋት ጠቅላይ ቤተ ክህነት ግቢን ለቅቀው እንደወጡ የቅርብ ምንጮች ገለፁ።የቅዱስ ሲኖዶስ የበላይነት አልቀበልም ብለው በማስፈራራትና በሀይል ጭምር አጀንዳውን ጠምዝዘው ጊዜያዊ እፎይታ ካገኙት ፓትርያርክ ጋር በገቡት አለመግባባት የግል ቂም ተይዞባቸው አደጋ የተጣለባቸው ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ሰሞኑን የጠቅላይ ቤተ ክህነትን ግቢ ለቅቀው የወጡ ሲሆን አንዳንዶች ወደ ሀገረ ስብከታቸው ወደ ወሎ መሄዳቸውን ሲናገሩ ሌሎች ደግሞ እዚያው አዲስ አበባ ከሰዎች ዘንድ ማረፋቸውን ተናግረዋል።“ ለሕይወቴ ደህንነት አይሰማኝም” እንዳሉ የተጠቆመው ብፁዕነታቸው ዕቃቸውን ጠቅልለው ሲወጡ መታየታቸው ሲዘገብ ሌሎች አባቶችም ቢሆኑ በተመሳሳይ የደህንነት ስጋት ላይ እንደሚገኙ ታውቋል። የደጀ ሰላም ምንጮች ጨምረው እንደተናገሩት የፓትርያርኩ ወዳጆች የተባሉት ሳይቀሩ በፍርሃት መያዛቸው ሲነገር ፓትርያርኩ ይቃወመኛል የሚሉት ላይ አደጋ ከማስጣል አይመለሱም የሚለው ጉዳይ እያደገ መምጣቱ ታውቋል።* [vii]

**የአቡነ ይስሀቅ ድንገተኛ ህመምና ሞት**

አቡነ ይስሀቅ ፓትርያርኩን ባደባባይ መውቀስ የማይወዱ እንደውም አንዳንዴ ከፓትርያርኩ ጎን በመሰለፍ ፓትርያርክ ጳውሎስን የሚደግፉ አባት እንደነበሩ የሚያውቋቸው ይናገራሉ። ምንም እንኳን ፓትርያርኩን ባደባባይ መውቀስ ባይወዱም በግል ግን ፓትርያርኩን ከክፉ ስራቸው ይመለሱ ዘንድ በተደጋጋሚ ይገስጿቸው ነበር። ይህ ያልተወደደላቸው የሚመስለው አቡነ ይስሀቅም በድንገት ታመው አረፉ ተባለ። አሟሟታቸውም እንደተለመደው ነበር። ምግብ ተጋበዙ ሆዴን ብለው ማቃሰት ጀመሩ። ከጥቂት ግዜያት በኋላ አረፉ።ዘገባው እንዲህ ይላል

> *ብፁዕ አቡነ ይሥሓቅ ከዕረፍታቸው ጥቂት ደቂቃዎች በፊት በቅዳሴ ከተሳተፉበት መንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም ተመልሰው ፓትርያርኩን ጨምሮ በመንበረ ፓትርያርኩ የመመገቢያ አዳራሽ ወደተገኙት አባቶች ዛሬ የሚዘከረው የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወርኃዊ በዓል መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ዝክር( ኀብስት) መላካቸው እና በጸሎታቸውም እንዲያስቧቸው መጠየቃቸው ተዘግቧል፡፡ ከውሎው ቅዳሴው መልስ የቀመሱት እህል እንዳልተስማማቸው እና ሕመም እንደሚሰማቸው የተናገሩት ብፁዕነታቸው ብዙም ሳይቆዩ ነው ሕይወታቸው ያለፈው፡፡* [viii]

**የመጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ሚስጥራዊ አሟሟት**

በሊቅነታቸው ወደር እንደሌላቸው የሚነገርላቸው መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ልክ እንደ አቡነ ይስሀቅ ፓትርያርክ ጳውሎስን ባደባባይ መናገር የማይወዱ ነገር ግን በግል አጥብቀው ፓትርያርኩን የሚኮንኑ እንደነበሩ ውስጥ አዋቂዎች ይናገራሉ። በተለይ ሁለቱን ሲኖዶስ አንድ ለማደረግ በሚደረገው እንቅስቃሴ ፓትርያርክ መርቆርዮስንም ክፉኛ በመተቸት ይታወቃሉ። ቢሆንም ግን ሁለቱን ሲኖዶሳት ለማስታረቅ ያቅማቸውን ደፋ ቀና ያሉ አባት ነበሩ። በቅዱስ ሲኖዶስ አባቶች በተደጋጋሚ

እንደተገለጸው ፓትርያርክ ጳውሎስ እርቁ እንዲመጣ ፈቃደኛ አልነበሩም። በሚደንቅ ሁኔታ እርቁን በሚመለከት ሲኖዶሱ ያሳለፈውን በጎ ውሳኔ ቃለ ጉባአ እስከመደበቅ መድረሳቸው በሰፊው ተዘግቦ እንደነበር ይታወሳል። ለ እርቁ መሳካት ከልባቸው ደፋ ቀና ሲሉ የነበሩት መጋቤ ብሉይም ሳያውቁት ጥላቻ ቀለበት ውስጥ ገቡ። ለ እርቁ ጉዳይ አሜሪካ ደርሰው እንደመጡ ህይወታቸው ድንገት አለፈ ተባለ።

> በትላንትናው ዕለት ረፋድ ላይ ለእርቅ እና ድርድር ጉባኤ የሄዱበትን የአሜሪካ ተልእኮ አጠናቀው አዲስ አበባ ቦሌ ዓለም ዓቀፍ አየር ማረፊያ እንደ ደረሱ ራሳቸውን የማቃጠል እና ልባቸውን የመውጋት ስሜት እንደተሰማቸው አብረዋቸው ለተጓዙት የልኡካን ቡድኑ አባላት የተናገሩት መጋቤ ብሉይ ሰይፈ፣ አስቸኳይ ሕክምና ሊያገኙ ይችሉ ከነበረበት ስፍራ ርቆ እና ከጊዜው ዘግይቶ አራት ኪሎ አካባቢ ቀድሞ ‹‹ጉድሸፐርድ›› አሁን ‹‹አዲስ የሕፃናት እና እናቶች ሆስፒታል›› በሚባለው የሕክምና ተቋም ውስጥ የመጀመርያ ደረጃ ምርመራ እየተደረገላቸው ሳለ ነበር ሕይወታቸው ያለፈው፡፡ ወዲያኑ አስከሬናቸው በቅዱስ ገብርኤል እና በዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታሎች ከፍተኛ ምርመራ ከተካሄደለት በኋላ ዛሬ ቀትር ላይ ሰበካቸው በሚገኙበት እና በአገልግሎት ብዙ በደከሙበት በቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን እንዲያርፍ ተደርጓል፡[ix]

**ማጠቃለያ**

በፓትርያርክ ጳውሎስ ዘመነ ፕትርክና ቤተክርስትያኗ በርካታ ሊቃነ ጳጳሳቷንና ሊቃውንቷን አጥታለች:: የሊቃነ ጳጳሳቱም ሆነ የሊቃውንቱ አሟሟት ተመሳሳይ ነው -ወይ በመኪና አደጋ ወይ ደግሞ በድንገተኛ ህመም:: ያረፉት ጳጳሳት በሙሉ ማለት ይቻላል በህይወት እያሉ ፓትርያርክ ጳውሎስን የሚቃወሙ ነበሩ:: ፓትርያርኩን አምርረው በተቃወሙ በጥቂት ግዜያት ውስጥ ሁሉም አለፉ:: ብዙዎቹ ሊቃነ ጳጳሳት የህልፈታቸው ምክንያት ምግብ ተጋብዘው ከበሉ በኋላ " ሆዴን " እያሉ ነው:: ጥቂቶቹም እስካሁን ግልጽ ባልሆነ መኪና አደጋ አልፈዋል:: ፓትርያርክ ጳውሎስን የተቃወሙ ሊቃውንት በሚያስገርምና ድንገተኛ ሁኔታ ህይወታቸው አልፏል:: የጎንደሩ ሊቀ ሊቃውንት በፓትርያርኩ አዲስ አበባ " ለመጽሀፍት ትርጓሜ" ተብለው ተጠርተው አዲስ አበባ በደረሱ በጥቂት ቀናት በድንገት አረፉ ተብሎ አስከሬናቸው ተጫነ:: ከህልፈታቸው በፊት እንደ ቤተክርስትያኗ ምሁርነታቸው ፓትርያርኩን አንደገሰጿቸው ይወሳል:: አለቃ አያሌው ታምሩም በፓትርያርኩ ሃምሳ ሶስት አመት ካገለገሉበት ቤተ ክህነት በግፍ ያለደሞዝና ጡረታ ተባረው በመጨረሻ አረፉ:: መጋቤብሉይም በድንገተኛ ህመም አረፉ ::

ሊቃነ ጳጳሳቱም ሆነ ሊቃውንቱ ህይወታቸው ከማለፉ አስቀድሞ ምእመኑን ተማጽነው ነበር:: አዲስ አበባ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ያለው ቤታቸው ሲሰበርና አደጋ ሲደርስባቸው " ደረሱልን" ብለው ነበር:: እነ አቡነ ቄርሎስም " ለህይወታችን እየሰጋን ነው" በማለት በተደጋጋሚ ተናግረው ነበር:: አቡነ መልኬጼዲቅም ከማለፋቸው አስቀድመው ህልፈታቸውን ተገንዝበውት እንደነበር የቅርብ ሰዎቻቸው ይናገራሉ:: ሌሎችም አንደዛው::

በስተመጨረሻም የዚህ ሁሉ ውዝግብ ምንጭ የሆኑት አባ ጳውሎስ ሊቃነ ጳጳሳቱት ተከትለው ወደማይቀረው የፍርድ ቦታ ሄዱ:: ይሄሁሉ ጦርነት ለዚህ ነበር:: እሳቸውም ስልጣናቸውን ክብራቸውን ገንዘባቸውን ጥለውት ሄዱ:: ተከትሏቸው የሚሄድ አምስት ሳንቲም ንብረት የለም:: በዚህች ምድር ላይ እያሉ የሰሩት ስራ ግን ተከትሏቸው ይሄዳል:: በጥይት ያስገደሉት ባህታዊ ነብስ በተለያየ ሴራ ያስፈጇቸው ጳጳሳትና ሊቃውንት ነብስ ግን በሄዱበት እየሄደ የፍርድ ያለህ ይላል:: የከፈሏት ቤተ ክርስትያን ፣ የመዘበሯት የቤተ ክርስትያን ንብረት ፣ ቅስሙን የሰበሩት የክርስትያን ነብስ ግን አሳት ሆኖ ይፈጃቸዋል::

በግፍ የተገደሉትን ሊቃነ ጳጳሳት በተመለከተ በርካታ ምእመናን እጅ በርካታ መረጃ እንዳለ ሁሉም ያውቃል:: በመርዝ አንጀታቸው እየተቃጠለ ያለቁትን አባቶቻችንን ቢያንስ ትውልድ ይዘክራቸው ዘንድ ቢያንስ ታሪካቸውን እንጻፍላቸው::

ወስብሀት ለ እግዚአብሔር

---

[i] አዲስ ነገር ጋዜጣ ግንቦት 2001 ዓ.ም እትም

[ii] ***http://www.ethioforum.org/?p=1081***

[iii] ***http://www.dejeselam.org/2009/05/blog-post_27.html***

[iv] ***http://www.dejeselam.org/2009/07/blog-post_16.html***

[v] ***http://www.dejeselam.org/2010/06/blog-post_21.html#more***

[vi] ***http://www.dejeselam.org/2011_05_01_archive.html***

[vii] ***http://www.dejeselam.org/2009/07/blog-post_25.html***

[viii] ***http://www.dejeselam.org/2011/03/1927-2003.html***

[ix] ***http://www.dejeselam.org/2010/08/blog-post_08.html***